ውድ የ APS ሰራተኞች እና ቤተሰቦች፡

እንደምታውቁት፣ የትምህርት ቤቱ ቦርድ አዲስ ዋና ተቆጣጣሪ መፈለግ ጀምሯል። በዚህ አስፈላጊ ሂደት ላይ የሚያግዘን BWP & Associates (BWP) የተባለ በዋና ተቆጣጣሪዎች ምልመላ ላይ ያተኮረ ብሄራዊ የፍለጋ ድርጅት አግኝተናል።

በዚህ ሂደት ውስጥ በጣም አስፈላጊው እርምጃ በአዲሱ ዋና ተቆጣጣሪያችን ላይ የምንፈልጋቸውን ባህሪዎች ለመለየት እና ለስራ መደቡ ጥልቅ መገለጫ ለማዳበር ከተማሪዎች፣ ከሠራተኞች፣ ከቤተሰቦች እና ከማህበረሰብ አባላት ጋር መተባበር ነው። BWP በተከታታይ የትኩረት ቡድኖች ውይይት እና የማህበረሰብ መድረኮችን እና የዳሰሳ ጥናቶችን በመጠቀም ግብዓት ለመሰብሰብ ከትምህርት ቤቱ ቦርድ ጋር አብሮ ይሠራል።

የትምህርት ቤቱ ቦርድ ሁሉንም የማህበረሰባችን አባላት በ BWP አማካሪዎች በተመቻቸ ስብሰባ ላይ እንዲሳተፉ ይጋብዛል። በጃንዋሪ 22 ወይም በጃንዋሪ 25 ቀን ከሚከተሉት ክፍት የማህበረሰብ መድረኮች ውስጥ በአንዱ ለመገኘት ይችላሉ ብለን ተስፋ እናደርጋለን።

- **ረቡዕ፣ ጃንዋሪ 22፣ በ 7 p.m. *(ስፓንኛ)***
  Kenmore መካከለኛ ደረጃ ት/ቤት፣ 200 S. Carlin Springs Road
- **ረቡዕ፣ ጃንዋሪ 22፣ በ 7 p.m.**
  Washington-Liberty ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት፣ 1301 N. Stafford Street
- **ቅዳሜ፣ ጃንዋሪ 25፣ በ 10 a.m.**
  Wakefield ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት፣ 1325 S. Dinwiddie Street
- **ቅዳሜ፣ ጃንዋሪ 25፣ በ 10 a.m.**
  Dorothy Hamm መካከለኛ ደረጃ ት/ቤት፣ 4100 Vacation Lane

እንዲሁም የዋና ተቆጣጣሪ ፍለጋን በሚመለከት የመስመር ላይ የዳሰሳ ጥናት ቅጽ በ APS ድር ጣቢያ በ www.apsva.us/engage/search-for-new-aps-superintenent/ ላይ **ከጃንዋሪ 21 እስከ ፌብሩዋሪ 2 ድረስ ይገኛል።** ጥናቱ ሲጀመር ለእርስዎ ለማሳወቅ በ School Talk በኩል ማስታወሻ እንልካለን።

በፍለጋ ሂደቱ ላይ የመስመር ላይ አስተያየት ቅጽ በማንኛውም ጊዜ በ https://www.apsva.us/engage/engage-aps-online-feedback/ ላይ በማስገባት ወይም ወደ engage@apsva.us ኢሜይል በመላክ የጽሑፍ ግብዓትዎን መስጠት እንደሚችሉ እባክዎ ልብ ይበሉ።

በዚህ በጣም አስፈላጊ ተግባር ላይ ለሚያደርጉት ድጋፍ በጣም ከፍ ያለ አድናቆት አለን እንዲሁም ለአርሊንግተን የህዝብ ት/ቤቶች ላደረጉት ድጋፍ እናመሰግናለን።

ከልባዊ ሰላምታ ጋር፣

Tannia Talento, ሊቀመንበር
Arlington School Board (የአርሊንግተን ትምህርት ቤት ቦርድ)